፫ኛ፤ ከግንቦት ፭ ቀን እስከ ነሐሴ ፴ ቀን ፬ት ወር ከ፩ት ከክሮስ ነውና አስተውሉ በ፬ት ወር ፩ድ ሰዓት በ፬ት ወር ፩ ሰዓት ሲሆን በ፲፬ት ወር ፫ ሰዓት ተሠር ቶበት አለፈ ማለት ነው በ፲፱፻፺፯ ዓ ም በዘመነ የ-ሐ ንስ ነሐሴ ፴ ቀን ፫ቱ ሰዓት ተሠርቶበት ያልፋል (ማስ ጠንቀቂያ) ፭ት ቀን ጳጉሜን ከከልኢት የተገኘ ስለሆነ ከክሮስና ከልኢት የለውም ከ፲፬ቱ ወር ብቻ ነው የሚ ቈጠረውና አስተውሉ ። በዘመነ ማቴዎስ ፲፯ ዓ ም እን ደዚሁ ፫ቱ ሰዓት ተሠርቶበት ያልፋል ። በዘመነ ማርቆስ ፲፰ ዓ ም እንደዚሁ ፫ቱ ሰዓት ተሠርቶበት ያልፋል። በዘመነ ሉቃስ ፲፱ ዓ ም እንደዚሁ ፫ቱ ሰዓት ተሠርቶበት ያልፋል ማለት።በ፲፱፻፺፱ ዓ ም በዘመነ ሉቃስ የስድስተኛዪቱ ጳጉሜን ቀኖር በነሐሴ ፴ ቀን ከላይ እንደተዘረዘረው ተስተስበ ሙሉ ፲፪ ሰዓት ይሆናል ።

ነገር ግን የነሐሴ ወር በ፱ኛው ዓመት ፴፩ ቀን መሆን ሲገባው የጥርቅም ቍጥር ስለ ሆነ ከ፩ቱ ቀን ጳጉሜን በኋላ ፯ኛ ቀን እንድትሆን ተደርጓል ከዚህ ውስጥ ያለ ማሻሻል ማስተዋል በቂ ነው ።

ከዚህ የቀረው በ፫ኛው መጽሐፍ ከ፫ኛ ክፍልና ከ፯ኛው ክፍል ተመልከት ።

ከመምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት ተዘጋጅ ተው የታተሙት መጻሕፍት ።

፩ኛ. የኤር ሡልጣንና ጎልጎታ የኢትዮጵያ ገዳም አስ ረጅ በኢየሩሳሌም በ፲፱፻፺ ዓ. ም.

፪ኛ. ርትዕት ይእቲ ሃይማኖቶሙ ለቅዱሳን አበዊነ በ፲፱፻፺፪ ዓ. ም.

፫ኛ. ስለ ኤር ሡልጣን የኢትዮጵያ ርስትነት በ፲፱፻፺፫ ዓ. ም.

፬ኛ. ፭ኛ. መጽሐፍ ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው በ፲፱፻፺፭ ዓ. ም. ታትሟል ።

፮ኛ. ፯ኛ. መጽሐፍ ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው ። በ፲፱፻፺፮ ዓ. ም. መስከረም ፯ ቀን ።

www.ethiopianorthodox.org

ማ ረ ሚ ያ ፤

ግድፈት ፥	እርም ፤	ገጽ	ክፍል
ሠርቀ ዕለትን ማግ ኘት ፤	ሠርቀ ዕለትን ለማግ ኘት ፥	፲	፫
ጳጉሜን ፭ ቀን ተርፍ አለች ፤	፭ ቀን ትተርፋለች ፤	፲፯	፯
ነነዌ ከዋለበት ሳኒ ታ አንሥተህ እስከ ነነዌ ፤	መጥቅዕ ከዋለበት ሳኒታ አንሥተህ እስከ ነነዌ ፥	፳፩	፰

ዲያቆን ሰሎሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes

www.ethiopianorthodox.org

ቁጥር 5407

ዲያቆን ሰለሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes

ማ ሻ ሻ ል

የተለመደ ሕግ ነው ።

ከመምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት ።

የሦስተኛ ደረጃ ትምህርት ቮኛ መጽሐፍ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በነገሡ በ፴፪ኛው
ዘመነ መንግሥት በ፲፱፻፷፯ ዓ ም ፣
ብፁዕ አቡነ ባስልዮስ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት የኢትዮጵያ ፓትረያርክ
በሆኑ በ፱ኛው ዓመት ፤
ይህ መጽሐፍ በትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

አዲስ አበባ ጎዳር ፭፱ ቀን ፲፱፻፷፯ ዓ. ም.

ዋጋው $ 1.25

www.ethiopianorthodox.org

መ ግ ቢ ያ

እ ና ሻ ሽ ል ።

ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው የቮተኛ ደረጃ ተምህርት ቮ ኛ መ ጽ ሐ ፍ ።

ይህ ጥንታዊው የሂሳብ መጽሐፍ ከኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ሲያያዝ የመጣ የእውቀት ምንጭ ስለሆነ ለመጭው ትውልድም ፈጽሞ ሳይጠፋ ስለ ተጻፈለት እውቀቱን በማስፋፋት እንደሚጠቀምበት የታወቀ ነገር ነው ። በኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ማንኛውም ነገር ማሻሻልና ማቃለል ደግ ነገርም መመሥረት ዋና ዓላማ ቸው እንደነበር ይህ መጽሐፍ በሰፊው ያስረዳናል በሃ ይማኖት ማሻሻል የለም እንጂ በሥራ ሁሉ ማሻሻል የጊዜውን ሁኔታ እየተከተሉ በሕዝብ ዘንድ ከበድ ብሎ የታየውን ሁሉ ማቃለል ሕዝብን ማስደሰት ከጠብና ከክ ርክር ከመነቃቀፍ እንዳይደርስ በሰላም መጠበቅ ፣ የተ ሠወረውም እውቀት ለመግለጽ የሚደክመው ወንድማ ችንን ረድተን ሐሳቡን ከግብ እንዲደርስ ማጽናናትና መደገፍ እንዲኖርብን ያስፈልጋል ።

ቮ ኛ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ በደግ ነገር ተነሥቶ ሲሠራ በምቀኝነት እንቅፋት ሆኖ ማስቀረት ተገቢ አይደለም ፣ ምቀኝነትም ክፍሉ የአጋንንት ነው ። ይህን ሁሉ መመሥረትና ማስወገድ የቤተ ክህነት ሥራ ነው የሚል ጥያቄ ይመጣ ይሆናል ነገር ግን ቤተ ክህነ ትን በመንቀፍ የምንጠቀምበት ነገር የለም መከተልና

ያለደራሲው ፈቃድ ማሳተም ክልክል ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

መመልከት የሚገባን ደጉ ንጉሠ ነገሥታችን ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ የመንግሥቱም የክህነቱም ሥራ እድገት አግኝቶ ሕዝብ እንዲጠቀምበት የሚደክሙትን ዓላማ መከተል በቂያችን ነውና ሁላችንም የተቻለንን ያህል መሥራት አለብን ።

ቮኛ ቤተ ክርስቲያን ስትባል ክርስቲያን ለተባልን ሁሉ ገንዘባችን ናት ፤ ወይም እንደ ስሟ ቤታችን ናትና በተቻለን መጠን በሥራም በሐሳብም ፣ ወይም እንደዚሁ በመጻፍም ሆነ ብንደክምላት ተደሰቱ የፈጠረን እግዚአ ብሔር ሲሆን ተጠቃሚው ሕዝብ ነው ስል በእውቀት አበባ አጊጦ ለሚታየው ትውልድ ሳበረክት ለወደፊቱ በአባቶቹ እውቀት ላይ መሥርቶ የበለጠ እውቀት እን ዲስፋፋበትና መነቃቀፍን ትቶ ማሻሻል እንዲኖርበት ከማሳሰብ ጋር ነው ለዚህም ድጋፍ የሚሆናችሁ ትን ቢታዊ ቃል አለ ፤ ዳንኤል ም ፲፪ ቁጥር ከ፫-፬ ብዙ ሰዎች ይመረምራሉ እውቀትም ይበዛል የሚለውን ዕድሉና ዕው ቀቱ ለእናንተ ይሁን አሜን ።

መሻሻል የተለመደ ሕግ ነው ።

ቮኛ መጽሐፍ የሦስተኛ ደረጃ ትምህርት ።

ቅዱስ ድሜጥሮስ በዓላትንና አጽዋማትን እንዲ ሻሻሉና በተወሰነላቸው ቀን ብቻ እየተዘዋወሩ እንዲ ውሉ ያደረገበት ምክንያት ሐዋርያትና ከሱ በፊ ትም የነበሩ ሊቃውንት በዓለ ትንሣኤ ከሰኞም ከማክ ሰኞም እስከ ቅዳሜ ይውል ነበርና ቅዱስ ድሜጥሮስ ነነዌ ጸመ ሐዋርያት ከሰኞ ፣ ፪ኛ. ደብረ ዘይት ሆሣዕና ትንሣኤ በዓለ ጰራቅሊጦስ ከእሁድ፤ባይወጣ ፡ ፍሥሕ ከሆሣዕና አን ሥቶ እስከ ቅዳሜ ሥዑር ባትወጣ ፡ ስቅለት ከዓርብ ባይ ወጣ ፡ ረክበ ካህናት ጸመ ድኅነት ከረቡዕ ባይወጣ ፡ ዕርገት ከሐሙስ ባይወጣ ፡ እወደ ነበር ብሎ ተመኝ፡ከዚህ በኋላ የታዘዘ መልአክ መጥቶ ነገር በምኞት ይሆናልን ? ያሰብ ኸው ነገር ሁኖልሃልና ሌሊት ፳፫ኛ ሱባዔ፡ቀን ፯ት ሱባዔ ያዝ አለው፤ ስለ ምን የሌሊቱን አበዛበት የቀኑን አሳነሰለት ቢሉ ሌሊት ዕረፍት ነውና ፤ቀን ግን የተጣላ ሲያስታርቅ የታመመ ሲጠይቅ ሲፈርድ ሲተች ይውላልና ስለዚህ የሌሊቱን አበዛበት የቀኑን አሳነሰለት ፡ የሌሊቱን ሲቈጥሩት ፻፷፭ ይሆናል፡በ፭ት ፴-፴ ሱባዔ ቢከፍሉት ፲፭ ይቀራል ፤ ይህ ጥንተ ሙላደ አበቅቱ ይባላል (መጀመሪያ አበቅቱ የተባለው የአጽዋማትና የበዓላት መቈጠርያ ከዚህ ተገኝ ማለት ነው) የቀኑ ፯ት ሱባኤ ፶፬ ይሆናል ፤ ፴ውን ገድፎ ፲፱ ይቀራል ይህ ጥንተ ሙላደ መጥቅዕ ይባላል ።

ዳግመኛም ሙላደ አበቅቱ በ፫፻ ፶፪ ቀን ነሐሴ (ማለት ነሐሴ ፳፬ ቀን) ጨረቃ ዓውደ ዓመትን ታደርሳለች ከነሐሴ ፯ት ቀን ከጳጉሜን ፭ት ቀን ፲፭ድ ይሆናል፡ዳግመኛ ሙላደ

www.ethiopianorthodox.org

አበቅቴ ይባላል ፤ መጥቅዕ ቢበዛ አበቅቴ ቢያንስ አበቅቴ ቢበዛ መጥቅዕ ቢያንስ ከ፴ አይወጣም ከ፴ አይወርድም ፤ በ፲፱፻፱ ቀን ጨረቃ ዓውዷን ታደርሳለች ማለት ከተነሣችበት ዙራ ትፈጽማለች ማለት ነው ፤ ዓውድ ማለትም ዙርያ ማለት ነው ።

ማሻሻል ተገቢ መሆኑን የሚያስረዳ መልአኩ ለቅዱስ ድሜጥሮስ ሌሊት ዕረፍት ስለ ሆነ ፷፫ት ሱባዔ ያገ አለው ። ቀን ግን የሥራና የድካም ሰዓት ስለ ሆነ ፤ ፯ት ሱባዔ ያገ አለው ።

ይህ የማሻሻል መምርያ ነው ሱባዔ ማለትም ፯ት ማለት ነው መሠረቱም ፯ቱ ቀኖች ናቸው (ወይም ስምንት ይባላል) በዚህ ጊዜ የማብዛትና የማከፈልን ሥራ ያስተምረናል ፤ ፯ት ጊዜ ፷፫ት ፬፻፺ ይሆናል ፤ ፬፻ውን ለ፴ ቀን ቢከፍሉት ፲፫ ፲፫ት ይደርሳል ትርፍ ፲፩ ቀን ይገኛል ። ይህ ከ፴ የተረፈው ቀን አበቅቴ ይባላል ፲፫ ፯ት ጊዜ ፯ት-፵፱ ይሆናል ይህ ለ፴ ቀን ቢከፍሉት ፩ድ-፩ድ ደርሶ ፲፱ ቀን ይተርፋል ፤ መጥቅዕ ማለት ይህ ከ፴ ቀን ትርፍ ሁኖ የተገኘ ነው ፤ መጥቅዕና አበቅቴ መሠረታቸው በወር ውስጥ የሚገኙ ፴ ቀኖች ስለሆኑ ከ፴ አይወጡም አይወርዱም ዘወትር ፴ ይሆናሉ ፤ ከ፭ኛው መጽሐፍ ከገጽ ፲፭ እስከ ፲፯ ተመልከት ።

፲፫ኛ ክፍል ።

ከዚህ የቅዱስ ድሜጥሮስን ታሪክ ባጭሩ እንጽፋለን ቅዱስ ድሜጥሮስ በግብርና የሚኖር ደግ ሰው ነበረ ። በወጣትነቱም ዘመን አሕዛብ በገዙት ነበርና አባቱና

እናቱ አስበው ከአሕዛብ ወገን እንዳያጋቡት ሃይማኖቱን እንዳይክድ ብለው የአጐቱ ልጅ የምትሆን አልፋ ወይን የምትባል ደግ ልጅ አጋቡት ። ለጊዜው የአባቱንና የእናቱን ትእዛዝ ሳይቃወም የጋብቻውን ሥነ ሥርዓት ፈጸመ ። ነገር ግን ሁለቱም ፍጹማን ደጋጎች ሰዎች ስለ ሆኑ በመንፈስ ቅዱስ ተጠብቀው ፤ በድንግልና ተወስነው ከ፭ ቤት ይኖሩ ነበር ። በዘመናቸውም የነበረ ሊቀ ጳጳሳት ቅዱስ ዮልያኖስ ይባል ነበር ። ለቅዱስ ማርቆስ ፲፩ኛ ነው ። ሸመገለና ሕዝቡ ተሰብስበው ሂደው አባታችን ሸመገልህ ከአንተ በኋላ የሚሾም ማነው? ንገረን አሉት ። እሱም ወደ እግዚአብሔር አመለከተና የታዘዘ መልአክ መጥቶ ከአንተ በኋላ የሚሾም ያለ ጊዜው የወይን ሸት ይዘልህ የሚመጣ ነው ብሎ ነግሮታል ። እሱም ለሕዝቡ ከእኔ በኋላ የሚሾም በተአምራት ያለ ጊዜው የወይን እሸት ይዘልኝ የሚመጣ ሰው ነው ብሎ ነግሯቸዋል ።

ቅዱስ ድሜጥሮስም ገበሬ ነውና ወደ አትክልት ቦታው ቢሄድ ወይኑ በተአምራት ያለ ጊዜው ለምልሞ ፤ አብቦ ፤ አፍርቶ አገኘው ። እያደነቀ ቁርጠ ወስዶ ለሚስቱ ሰጣት ። እሷም መንፈስ ቅዱስ ያደረባት ደግ ሰው ናትና በአዲስ አገልግል ለጉማ ፤ በሻሽ ሸፍና ፤ ይህ በተአምራት የተገኘ ነገር ለኛ አይገባንምና ወስደህ ለሊቀ ጳጳሳቱ ሰጥተህ ፤ ተባርከህ ና አለችው ። ይዘ ሄዶ ለሊቀ ጳጳሳቱ ሰጥቶ ፤ ተባርኮ እወጣለሁ ሲል ሊቀ ጳጳሳቱ ለሕዝቡ ከኔ በኋላ የሚሾም ይህ ነው ብሎ ነግሯቸው

www.ethiopianorthodox.org

አርፉል ። ሕዝቡም የበቃና ከእግዚአብሔር የተመረጠ መሆኑን አውቀው ሹመውታል ። በመንበረ ማርቆስ ከተሾሙት ድሜጥሮስ ፲፪ኛ ነው ። ታሪኩ ብዙ ነው በራሱ ገድልና በስንክሳር ተመልከት ።

አሁን ወደተነሣንበት እንመለስ ። የድሜጥሮስ አባትና እናት በማሻሻል ሃይማኖት ከሚፈርስ ምግባር (ማለት አስተዳደር) ይፍረስ ብለው የአጐቱን ልጅ እንዲያገባ ፈቅደው ድረውታል ። አሁን ግብጾች ይህን አብነት አድርገው እስከ ዛሬ ድረስ የአጐታቸውን ልጅ ፣ የአክስታቸውን ልጅ ያገባሉ ።

ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ግን ዝምድና እስከ ፯ት ትውልድ የሚከበር መሆኑን አውቀው ከአባቶቻቸው የቄየ ሥርዓት አለወጡም ። የኢትዮጵያ ሕዝብ ከጥንት ጀምሮ ከቅድስና ወደቅድስና ፣ ከዕውቀት ወደዕውቀት እየተራመደ የሚሄድ አዋቂ ሕዝብ ነው የምንልበት ፩ኛው ይህ ነው ። ደኅናውን ዕውቀት ተቀብሎ ተገቢ ያልሆነውን መተው ለኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ዋና ተግባራቸው ነው ። እኛም እንደ አባቶቻችን መሆን አለብን ።

የአስተዳደር የሥራ ሁኔታ ይሻሻላል ፣ ሃይማኖት ግን መሠረት ነውና አይሻሻልም ፣ ይኸውም በድሜጥሮስ አባትና እናት በዘመናቸውም የነበሩ አበው የሠሩበትን ከላይ እንደገለጽነው ያስረዳል ።

፫ኛ ክፍል ።

ከዚህ ቀጥሎ ያለው ትምህርት ምንጩ ስንመለከተው የአየር ምርመራ የሳይንስ የፍልስፍና የሊሳብ ሁኔታ አጣምሮ የሚያስረዳ ጥንታዊ ትምህርት ነው ፣ ከዚህ በፊት በ፪ኛው መጽሐፍ በ፱ኛው ክፍል ከገጽ ፲ ላይ ጳጉሜን መጀመሪያ መደቡ ፱ት ነው ብለን ነበር አሁን ግን ጳጉሜን በዓመት በዓመት ፭ት የምትሆንበትን ምክንያት ከዚህ እንረዳለን ፣ ፭ኛ ዐሐይ በቀን ከጨረቃ በልጣ የምታበራው ፉድ ኬክሮስ ፱፪ት ከልኢት ፴፭ደ ፵ሊሲት ነው ፣ የቀን ፭ደ ፭ደ ኬክሮስ እስከ ፴ ቀን ፴ ኬክሮስ የ፪ት ወር ፶ ኬክሮስ ፭ደ ቀን ይሆናል ፣ የ፲፪ት ወር ፯ት ቀን ይሆናል ፣ ይህ ከ፭ደ ኬክሮስ የተገኘ ፯ ቀን ሕዐጽ ብለው የሌሊት መቁጠርያ አድርገውታል ። ፪ኛ በቀን ፶፪ት ከልኢት እስከ ፴ ቀን ቢቈጥሩ ፲፭፻፭— ይሆናል ፣ በ፷ በ፷ ቢከፍሉት ፵፯ት ኬክሮስ ይሆናል ። ፵፯ት ኬክሮስ በ፲፪ት ወር ፫፻፲፪ት ኬክሮስ ይሆናል ። ፫፻፩ውን በ፷ በ፷ ቢከፍሉት ፭ ቀን ይሆናል ፣ በዓመት ፭ ቀን ከ፲፪ት ኬክሮስ ይሆናል ፣ ይህ ፭ ቀን ጳጉሜንና ፲፪ት ኬክሮስ ከ፶፪ት ከልኢት የተገኘ ነው ።

ከልኢት ማለት ሁለተኛ ማለት ነው ፣ በሥልጣኔው ዘመንም ሰከንድ ይባላልና ይህ ጥንታዊውን አቈጣጠር ፉሣ አድርገን እናስተውለው) ፫ኛ ከ፭ደ ቀን የተገኘ ፴ሰደ ሚልሲት እስከ ፴ ቀን ቢቆጥሩ ፱፻፴ ሚልሲት ይሆናል ፱፻፩ውን በ፷ በ፷ ቢከፍሉት ፲፭ት ከልኢት ከ፴ ሚልሲት ይሆናል አሁንም ፲፭ት ከልኢት

www.ethiopianorthodox.org

ማሳሰቢያ ።

ፀሐይ በቀን ከጨረቃ በልጣ የምታበራው ብለን ተነ
ሥተን ሁኔታውን ዘርዝረን አስረድተናል፤ ነገር ግን ጨረቃ
በሙላት ጊዜ ፲፪ት ሰዓት በምታበራበት ቀን ነው እንጂ
ከመባቻ እስከ ፴ ቀን ያለው ብርሃኗ አይደለም ፤ በየጊዜው
ከመቀነስዋም በላይ ፈጽማ ሳታበራ የምታድርበት አለና
አስተውሉ ።

፬ኛ ክፍል ።

ከዚህ ቀጥሎ ያለው ጽሑፍ በጣም የረቀቀ ነገር
የሳይንስን ሁኔታ የሚያስረዳ ነው በ፫ኛው ክፍል እንደ
ተጻፈው ከ፴፭ድ ሣልሲት በዓመት የተገኘ ትርፍ ቍጥር
፯ት ካልኢት አለ፤ ይህ በዓመት የሚገኝ ፯ት ካልኢት እረና
መዓልት የምትባል በ፯፪ ዓመት የምትገኝ ፯ተኛ ጳጉ
ሜን የምትገኝበት ቀኖር ፤ ነው በ፲ ዓመት ፭ድ ኬክሮስ
ይሆናል ፤ (ማለት በ፲ ዓመት ፮ ካልኢት ፭ድ ኬክሮስ ይሆ
ናል ማለት ነው) በ፻ቶ ዓመት ፲ ኬክሮስ ሲሆን በ፯፪ ዓመት
፮ ኬክሮስ ይሆናል ። ፮ ኬክሮስም ፭ድ ቀን ነውና እረና
መዓልት የምትባለው ፯ተኛ ፤ ጳጉሜን አለች ይላሉ አባ
ቶቻችን እስከ ዚህ ተራቅቀው መርምረው በጽሑፍ አስ
ረድተዋል፤ (ሆኖም ይህችን ዕለት በቃል አሥረዱ እንጂ
ከቍጥር የገባችበትን ቀን አላስረዱም ። ሲያስረዱም ዓለም
በዚህች ቀን ታልፋለች ይላሉ ፤ ይህ በጣም የረቀቀ ነገር
ነው) ምክንያቱም ሲያስረዱ ይህች ቀን ማለት እረና መዓ
ልት የተባለችው (ትክክለኛ ቀን) ትክክለኛነቷም ፭ደኛ ንኡስ

በ፲፪ት ወር ፪፹ ካልኢት ይሆናል ፤ ፴ው ሣልሲት በ
፪ት ወር ፫፻፷ ሣልሲት ይሆናል ፤ ፪፹ውን ካልኢት በ፯
በ፭ ቢከፍሉት ፫ት ኬክሮስ ይሆናል ፤ ፫፻፷ውን ሣል
ሲት በ፭ በ፭ ቢከፍሉት ፯ት ካልኢት ይሆናል በዓ
መት ከ፭ ቀን የተገኘ ፴፭ድ ሣልሲት ፫ት ኬክሮስ
ከ፯ት ካልኢት ይሆናል (ሣልሲት ማለት ሦስተኛ ማለት
ነው ፤ በዛሬው ሥልጣኔም የሰከንድ ሰከንድ የሚባለው
ይህ ነው) ፬ኛ አሁን በዓመት ውስጥ ስንት ቀኖችና
ስንት ኬክሮስ እንዲሁም ስንተ ካልኢት እንዳገኘን
እንመልከት ፭ኛ ከ፭ድ ኬክሮስ የተገኘ ሕፀፅ የተባለው
፯ት ቀን ፪ኛ ከ፶፪ት ካልኢት የተገኘ ፩ ቀን ጳጉሜንና
፲፪ት ኬክሮስ ፫ኛ ከ፴፭ድ ሣልሲት የተገኘ ፫ት ኬክሮ
ስና ፯ት ካልኢት መሆኑን ተረድተናል ፤ (ኬክሮስ ማለት
፲፪ት ደቂቃ ማለት ነው ።

አሁን ወደ ሥድስተኛዪቱ ጳጉሜን ሁኔታ እንሂዳለን፤
፯ቱ ጳጉሜን በ፬ኛው ዓመት የምትገኝበት ምክንያት
ከ፭ድ ዓመት ውስጥ ከ፶፪ ካልኢት የተረፈ ፲፪ት ኬክሮስና
ከ፴፭ኛ ሣልሲት የተገኘ ፫ት ኬክሮስ ፲፭ት ኬክሮስ ይሆ
ናል (፲፭ቱ ኬክሮስ ፫ት ሰዓት ማለት ነው) ሥድስተኛዪቱ
ጳጉሜን ፲፭ት ኬክሮስ ከዮሐንስ ፲፭ት ኬክሮስ ከማቴዎስ
፲፭ት ኬክሮስ ከማርቆስ ፲፭ት ኬክሮስ የሉቃስ ነው ፤ የ፬ቱ
ዓመት ፮ ኬክሮስ ፭ድ ቀን ይሆናል ፤ ፯ኛዪቱ ጳጉሜን
በ፬ኛው ዓመት የምትገኝባት ይህ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

በ፮፻፩ዱ ዓመት ፮ ከክሮስ ይሆናል
፮ ኬክሮስም ፲፪ት ሰዓት ነው ።
፲፪ ሰዓትም ፭ ቀን ነው ።

ወይም የቀኑና የሌሊቱን ሲቈጠር ፲፭ ኬክሮስ ይሆናል ፤ ፲፭ ኬክሮስም ፺፬ት ሰዓት ይሆናል ፤ ፺፬ት ሰዓትም ፭ድ ቀን ነው ፤ አሪና መዓልት የተባለችው ፯ኛ ጳጉሜን በዚሁ ሂሳብ ትገኛለች ሲሉ ከቅዱስ ድሜጥሮስ ዘመ ነጩው የሂሳብና የማሻሻል ድርጅት መሠረት አባቶቻችን ኢትዮጵያውያን የእውቀት መዝገባቸውን ለልጅ ነቸው አውርሰዋል ።

ሆኖም ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን እውቀታቸው ከቅዱስ ድሜጥሮስ ብቻ የወረሱት አይደለም እውቀ ታቸው ከዘመነ ብሉይ ሲያያዝ የመጣ ነው ፤ (የዚህም መግለጫ በሚከተለው ክፍል እናስረዳለን) የምጽአትን ነገር ለማወቅ ከድሜጥሮስ በፊት ብዙ የተደከመበት መሆኑና በፍጡርም እውቀት ሊወሰን የማይቻል መሆኑን ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ባሥራ አስረድቷል ። ማቴዎስ ም ፳፬ ቁ ፴፮ ወበእንተ ይእቲሰ ዕለት ወይእቲ ሰዓት አልቦ ዘየአምራ ኢመላእክተ ሰማይ ፤ ወኢወልድ ዘእን በለ አብ ባሕቲቱ ብሏል ፤ ስለዚያች ቀንና ስዐዚያች ሰዓት ግን ከአባት ብቻ በቀር የሰማይ መላእክትም ቢሆኑ ልጅም ቢሆን የሚያውቅ የለም ፤ የሚለውን አምላካዊ ቃል ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ተገቢ ባልሆነው ምር መራ ሊጋፉ አልፈቀዱምና የዚህች ቀን ቀኖጥር ዓዋጁን

ቀመር ሙሉ ሲሆን ማለት ፲፱ኛው ዓመት ፀሐይና ጨረቃ ዙረው ሲገናኙ ፤ ፱ኛ ወንጌላዊ ዮሐንስ ሲሆን ፤ ፫ኛ ወሩ መጋቢት ቀኑ አሁድ ሲሆን ፤ ፬ኛ አሪና መዓልት ልክ በ፮፻፱ ዓመት ስለምትገኝ ይህች ቀን ሐምትውልበት ዘመን ፬ቱም ሲተባበሩ ዓለም ታልፋለች ሲሉ ያስረዳሉ ። ነገር ግን እነዚህ የሚገናኙበት ቀን እስከ ብዙ ሽህ ቢቈጥሩ በፍጡር ሐሊና ተመርምሮ ሊወሰን ፤ ወይም ሊደረስበት አለመቻሉን አውቀው የኢትዮጵያ ሊቃውንትና ቅዱሳን ዓዋጁን ይናገራሉ እንጂ ውሳኔ አልሰጡበትም ፤ ይህም ትምህርት የሳይንስ ምንጭ ነው ለማለት ያስደፍራል ።

ወይም የሂሳብ እስከ ፍራክሽን ፤ እንደዚሁም የሰዓት አቈጣጠር እስከ ሰከንድ ያሉ ሁሉ ምንጫቸው ነው ብን ልም እንችላለን ፤ ስለሂሳብና ስለ ሰዓት አቈጣጠር በጣ ልሲት ይጀምራል (ጣልሲት ማለትም በሥልጣኔው ጊዜ የሰከንድ ሰከንድ ማለት ነው ።

በቀን ፭ ጣልሲት ፭ድ ÷ ፴ ብናበዛው ፴ ይሆናል፣ ፴ × ፲፪ (በዓመት) ፫፻፷ ጣልሲት ይሆናል ፤ ፫፻፷—፯ ፶ ፶ ይደርሳል ፤ ፶ ጣልሲት ፭ድ ካልኢት ነው፤ (ካልኢት ማለትም ፣ የሰከንድ ሰከንድ ማለት ነው) በአንድ ዓመት ውስጥ ከጣልሲት የተገኘ ፯ ካልኢት ይሆናል ፤ ፯ት + ፲ ፶ ካልኢት ይሆናል ፤ ፶ ካልኢት ፭ ኬክሮስ ይሆ ናል ፤ (፭ድ ኬክሮስም ፲፪ት ደቂቃ ነው) በ፲ዶ ዓመት ፲ ኬክሮስ ይሆናል ።

www.ethiopianorthodox.org

ተናግረው ዕለቲቱን (ቀኒቱን) ከዓመታት አግብተው አል ቈጠሯትም ።

ነገር ግን ይህች ቀን ከልደተ ክርስቶስ በፊት ፱ ቀን ከ፲ ኬክሮስ ሁና ነበር ማለት ከሏሺሕ ከ፬፪ ዘመን ውስጥ ፱ ቀን ይገኛል ፤ በ፪ቶ ዓመትም ፲ ኬክሮስ ይገኛል ማለት ነው ፤ ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ እስከዛሬ ድረስ ማለት እስከ ፲፱፻፺፯ ዓ. ም. ፫ ቀን ከ፲፭ ኬክሮስ ከ፴፯ት ከል ኢት ሆናለች ማለት በሽሕ ፷፪ ዓመት ውስጥ ፫ ቀን ይገኛል ።

በ፱፻፺፮ ዓመትም ፲፭ ኬክሮስ ከ፴፯ ከልኢት ይገ ኛል ማለት ነው ፭ ማልሲት ፭×በ፴ ሲበዛ ÷ ፴ ይሆናል ። ፴ውም በ፲፱ ሲበዛ ፫፻፷ ይሆናል ። ለ፮ ÷ በ፷ በ፷ ቢከፍሉ ፮ ከልኢት ይሆናል በ፭ ዓመት ውስጥ ከ፭ ማልሲት የተገኘ ፮ ከልኢት ይገኛል ማለት ነው ። ፮ ከልኢት ፮×በ፲ ዓመት ሲበዛ ፷ ከልኢት ይሆናል ፷ ከልኢትም ፭ ኬክሮስ ነውና አስተውሉ ።

ከዚህ ቀጥለን ዝርዝሩን በዘመናዊው ስም በየአ ንዳንዱ ሁኔታውን እንገልጻለን ። ፭ድ ማልሲት (በጥንቱ ፭ድ ተኩል የሰከንድ ሰከንድ ነው) በሐዲሱ ግን ፫ የሰ ከንድ ሰከንድ ይሆናል ፷ያው ማልሲት ፴ የሰከንድ ሰከ ንድ ÷ በሐዲሱ ፷ ይሆናል ፷ውም ፭ ሰከንድ ነው ።

፱ኛ፤ ፭ ከልኢት በጥንታዊው ፫ ሰከንድ ነው ። በዘ መናዊው ሥልጣኔ ግን ፮ ነው ።

፫ኛ፤ ፭ ኬክሮስ በጥንታዊው ፮ ደቂቃ ነው ። በሐ ዲሱ ሥልጣኔ ግን ፲፱ ነው ።

፷ ማልሲት የሰከንድ ሰከንድ ፴ ይሆናል ፴ውም ፭ ሰከንድ ነው ፷ ማልሲት ፫ ሰከንድ በጥንታዊው በሐ ዲሱ ፮ ሰከንድ ነው ማለት ፭ድ ከልኢት ነው ። ፭ድ ከልኢት በጥንታዊው ፫ ሰከንድ በሐዲሱ ፮ት ሰከንድ ነው ፫×፲ ÷ ፴—(ወይም ፮×በ፲ ÷ ፷ ይሆናል ፷ውም ፭ድ ከንትሮስ ይባላል (ይሆናል) ፷ ከልኢት ፮ት ከንትሮስ ይሆናል ፩ድ ከንትሮስም በጥንታዊው ፭ ደቂቃ በሐዲሱ ፱ት ደቂቃ ማለት ነው ፮ቱ ፮ት ደቂቃ (ወይም ፲፱ ነው ።)

፭ድ ኬክሮስ በጥንታዊው ፮ ከንትሮስ ማለት ፮ ደቂቃ በሐዲሱ ግን ፲፱ ደቂቃ ነው ። ፮×፭ ÷ ፴ በጥንታዊው ፲፱×፭ ÷ ፷ በሐዲሱ ፭ ኬክሮስ በጥንታዊው ፴ በሐዲሱ ፷ ደቂቃ ስለሆነ ፭ ሰዓት ነው ።

በጥንታውያን አባቶቻችን ዘመን ፭ዱ ሰዓት ከአም ስት ይከፈል ነበር ማለት ነው ። ነገር ግን ዛሬ በምዕራባ ውያን ተሻሽሎ በተወሰነው የሰዓት አቈጣጠር በ፮ ወይም በ፲፱ ደቂቃ ይከፈል የነበረውን አሻሽለው በ፲፭ ደቂቃ ስለከፈሉት ፭ዱ ሰዓት ከ፱ ተከፍሏል በዚሁም ጸንቶ ይሠ ራበታል ይኸ በመሻሻል የተቃና ሥራ ነውና እናስተ ውለው ።

(የጥንት ቍጥሮች) ፩ኛ፤ ፷ ማልሲት ፭ድ ከልኢት ነው ፱ኛ፤ ፷ ከልኢት ፭ድ ኬክሮስ ነው ።ወይም ፮ ከንትሮስ ይባላል ፫ኛ፤ ፭ ኬክሮስ ፭ድ ሰዓት ነው (ወይም ፴ ከንትሮስ ነው) ከን

www.ethiopianorthodox.org

መጥቅዕና አበቅቴ ከቅዱስ ድሜጥሮስ ወዲህ እንጂ ከዚያ በፊት በዘመነ ብሉይ መቼ ነበረ ለሚል ሰው መልሱን ከዚህ በታች ያለውን ቀኖጥር ማስረጃ እንሰጣለን።

በጥንታውያን አባቶቻችን ቀኖጥር ንኡስ ቀመር ራሱ መጥቅዕ ነው ። ቀኖጥሩም ፲፱ ዓመት ነው ። በዚሁም መሠረትነት አበቅቴ ይገኛል ። ይኸውም ዕሪና መዓልት የተባለችው ፯ኛ ጳጉሜን በ፯፻ ዓመት መጨረሻ ስለም ትገኝ ። ፯፻ውን ዓመት ለ፲፱ ንኡስ ቀመር ቢከፍሉት ፲፩ ይተርፋል ማለት (ማለት ፴፩ ንኡስ ቀመር ሆኖ ፲፩ድ ዓመት ይተረፋል ማለት ነው) ዋናው ሙላደ አበቅቴ ይህ ነው ይባላል ፲፱ና ፲፩ ፴ ይሆናል ። የመጥቅዕና የአበቅቴ መሠረታቸው ይህ ነው ።

አከፋፈሉም ይህን ተመልከት

$$\frac{\text{፴፩}}{\text{፯፻}} \div \text{፲፱}$$

$$\frac{\text{፭፻፸፰}}{\text{፴}}$$

$$\frac{\text{፲፱}}{\text{፲፩}}$$

አበቅቴ

ከ፯፻ ዓመት ፭፻፸፱ ዓመት ÷ ፴፩ድ ንኡስ ቀመር ይሆናል ። ትርፉ ፲፩ድ ነው ። ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን በዘመነ ብሉይ የተሠሩ አጽዋማትና በዓላት መሠረታቸው መጥቅዕ ነው ያሉበት ምክንያት ይህ ነው ። ኢትዮጵያውያን አስቀድመው ከአባቶቻቸው ያገኙትን

ትሮስም ደቂቃ ማለት ነው ደቂቃም(በዓረብኛው የተሰባበረ ወይም ዶቂት ማለት ነው) አባቶቻችንም ጥቃቅን ይሉት ነበር አሁን ግን ደቂቃ ተብሏልና እናስተውል ። አሁን የ፱ቱን ቍጥሮች ሁኔታ እናሳያለን ። ከንትሮስ የደቂቃ ቁጣሪ ምልክት ነው ፣ ፴ ከንትሮስ ፩ ሰዓት ነው ፣ ወይም ፭ ኬክሮስ ነው ። ኬክሮስም የሰዓት ቁጣሪ ምልክት ነው ። ፭ ኬክሮስ ፩ድ ሰዓት ነው ፣ ወይም ፺ ኬክሮስ ፲፱ ሰዓት ነው ። ፯ ከንትሮስ ፩ ኬክሮስ ነው ፣ ፭ ኬክሮስም ፩ድ ሰዓት ነው ። ፴ ከንትሮስ ፭ ኬክሮስ ይሆናል ፣ ፭ት ኬክሮስም ፩ድ ሰዓት ነውና እናስተውል ።

፭ኛ ክፍል ።

ስለ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ዕውቀት በ፬ኛው ክፍል ዕውቀታቸው ከቅዱስ ድሜጥሮስ ብቻ የወረሱት አይደለም ። ከዘመነ ብሉይ ሲያያዝ የመጣ ነው እንጂ ያልንበትን ምክንያት እንገልጻለን ።

በዘመነ ብሉይ የተሠሩ አጽዋማትና በዓላት መሠረታቸው መጥቅዕ ነው ሲሉ ፣ ወደላይ ሲወጡ የሚሉበትን ፣ ወደታች ሲወርዱ የሚሉበትን መመላለሻቸውን በመጥቅዕ መሠረትነት ወስነው ፣ አስተምረው በደንብ ጽፈው ታል ። ይህ ጽሑፍ በዘመነ አሪት ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን መጥቅዕና አበቅቴን ፣ ዘመናትና በዓላትን እንደዛሬ ይቈጥሩበት ነበር ማለት ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

የተነጋገረውና በፍጻሜውም መጠመቅ የሚከለክለኝ ማን አለ አጥምቀኝ ብሎ ሲያዘው እንዳጠመቀው ያስረዳናል ይህ የኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የደግነታቸውና የዕውቀታቸውን መጠርግ የሚያስረዳ ነው ለማለት ያስችለናል። በቅዱስ ድሜጥሮስም ጊዜ በሀገራቸው ላይ የደረሰው ችግር ምክንያት ጥንታውያን መጻሕፍት በመታጣታቸው ልዩ ልዩ ችግር እንደደረሰባቸው የታወቀ ነው ይህ ቅዱስ ከእግዚአብሔር በተሰጠው ኃላፊነት ወደ እግዚአብሔር አመልክቶ ያገኘውን ጸጋ ወንድሞቹ ምዕመናንን ጠቅሞ በታል ። የኢትዮጵያ ሊቃውንትም ከጥንታዊው ባህላቸው ተስማሚ ሁኖ ስላገኙት ተቀብለው ሠርተውበታል። ኢትዮጵያ ምንጊዜም የሠለጠነች አገር ናት እንጂ የውጭ ባዕድ አሠልጣኝ የለባትም እንላለን ።

፯ኛ ክ ፍ ል ።

ከኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የቂየ የዘመነ ብሉይ በዓላትና አጽዋማት አቁጣጠር ቀጥሎ ያለው ነው ።

ኢየዓርግ ፡ ኢይወርድ ፡ መመላለሻውን ይናገራል ። ፲፮ መጥቅዕ ሲገኝ በዓለ መጥቅዕ መስከረም ፲፮ ቀን ዓርብ ሲውል ነው ። ኢየዓርገ ፲፫ት መጥቅዕ ሲገኝ በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት ፲፫ ቀን ቅዳሜ ሲውል ነው ። ፲፫ና ፲፮ ጽጌ ይሆናል የመጥቅዕ መመላለሻው ይህ ነው እንደምን ቢሉ መስከረም ዓርብ ሲሆት በዓለ መጥቅዕ መስከረም በባተ በ፲፮ኛው ቀን ዓርብ ቢውል አጽዋማት በዓላት በታችኛው ቀናቸው ይውላሉ ።

መስከረም ቅዳሜ ሲሆት ጥቅምት ሰኞ ይበታል ።

እውቀት መሠረት አድርገው የቅዱስ ድሜጥሮስም ድርሰት (ወይም ድርጅት) ከዚሁ ያልተለወጠ ጥንታዊውን መሠረት ያልለቀቀና ድርጅቱም በዘመነ ሐዲስ ለተሠሩ በዓላትና አጽዋማት መመላለሻቸውን ደንግጎ የወሰነውን ውሳኔ ተቀብለው አስተምረውበታል እንጂ በኢትዮጵያ ጥንት ያልታወቀ በአዲስ አሠልጣኝ መልክ የተቀበሉት አይደለም ። ኢትዮጵያውያን በየጊዜው መጀመሪያ በተሰጣቸው ደግነት ከእግዚአብሔር አግኝተው ተመሳሳዩን መርምረው በማጽደቅ ይሠሩበታል እንጂ አስቀድመው ያላወቁትን በአሠልጣኝነት አዲስ መምህር ገብቶ ያሠለጠናት ማንም የለም ። ለዚሁም ማስረጃ ብንፈልግ የኢትዮጵያ ነገሥታት እናት ፡ ንግሥተ ሳባ በሰሎሞን ዘመነ መንግሥት ከአባቶችዋ ባገኘችው እውቀት ተመራምራ ራሷ መሪ ሁና ከሰሎሞን ጋር የተናገረችው ቃል በቂ ነው ነገሥት ፩ኛ፲ ፲ ቊጥር ፩ ፱ አንተን የወደደ በእስራኤልም ዙፋን ያስቀመጠህ አምላክ እግዚአብሔር የተባረከ ነው ስትል አስረድታው አለች ፡ ይህ ለኢትዮጵያውያን እናቶችና አባቶች አንደኛ ክብራቸው ነው ። ፪ኛ፲ ዘዘመነ ሐዲስ እንደዚሁ በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የክብር ክብር እንደተሰጣት ግልጽ ነው ይኸውም ማቴዎስ ም፲ ፲፪ ቊጥር ፵፪ ንግሥተ አዜብ የሰሎሞንን ጥበብ ለመስማት ከምድር ዳር መጥታለችና ከዚህ ትውልድ ጋር በፍርድ ቀን ትነሣለች የሚለውን እንመልከት ፫ኛ፲ የሐዋርያት ሥራ ምዕራፍ ፰ ቊጥር ፳፯ ስለ ሀንደኬ የኢትዮጵያ ንግሥት አዛዥ የነበረ ከሐዋርያው ፊልጶስ ጋር

በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት ፲፬ተ ፲፫ኛው ቀን ቅዳሜ ቢውል አጽዋማት በዓላት በላይኛው ቀናቸው ይውላሉ።

የአጽዋማተ አሪት ተውሳክ መጥቅዕ የዋለበት ፲፩ኛ ውን ቀን ትቶ ከ፲፯ ቀን እንሥቶ እስከ ጾመ አይሁድ ያለው ቀን ፱ ይሆናል ። የጾመ አይሁድ ተውሳክ ይህ ነው ። ሁልጊዜ መጥቅዕ ሲዘዛ ሲያንስም መጥቅዕ የዋለ በትን ትቶ ቢቆጥሩ እስከ ጾመ አይሁድ (ቢቆጥሩ) ፱ ቀን ይሆናል ጠቅላላው ቦዚሁ ዓይነት ይወጣል ። መጥ ቅዕ የዋለበትን ትቶ ከ፲፯ ቀን እስከ ጾመ መጸለት ፲፬ት ይሆናል የመጸለት ተውሳክ ይህ ነው ። ከ፲፯ ቀን እስከ ፍሥሐ አሪት ፱፯ ቀን ይሆናል ። ፱፫ውን ለ፯ት በ፴ በ፴ ቢከፍሉት ፲ ይተርፋል የፍሥሐ አሪት ተውሳክ ይህ ነው ከ፲፯ ቀን እስከ ልብ ምድር ፹፱፲፫ት ይሆናል ፹፱፲፩ን ለ፯ት በ፴ ቦ፴ ቢከፍሉት ፫ ይቀራል የልቡ ምድር ተው ሳክ ይህ ነው ። ከ፲፯ ቀን እስከ በዓለ ሰዊት ፹፱፵ ይሆ ናል ፹፱፲፩ን ለ፯ት ቦ፴ በ፴ ቢከፍሉት ፴ ይተርፋል የበዓለ ሰዊት ተውሳክ ይህ ነው ። ከ፲፯ ቀን እስከ ጾመ አስቴር ፫፻፵፩ ይሆናል ። ፫፻፱ውን ለ፲ በ፴ በ፴ ቢከፍሉት ፵፩ ይቀራል የጾመ አስቴር ተውሳክ ይህ ነው ከ፲፯ ቀን እስከ ጾመ ዮዲት ፫፻፵፯ት ይሆናል ። ፫፻፱ውን ለ፲ በ፴ በ፴ ቢከፍሉት ፵፯ ይቀራል የጾመ ዮዲት ተውሳክ ይህ ነው ። ይህ ፱ቃችኛው ቀናቸው የሚ ውሉበት ነው የላይኛው ቀናቸው ግን ፲፫ መጥቅዕ ስለሆነ የቀሩጥሩ መነሻ ከጥቅምት ፲፬ ቀን እንሥቶ እን ደላይኛው መቀሩጠር ነው የአጽዋማተ ብሉይ የበዓላተ

ብሉይ ተውሳክ የሚገኘው በመቅዕ ብቻ ነው ። ከዚህ ቀጥሎም መመላለሻቸውን ይናገራል ።

፩ኛ የጾመ አይሁድ ተውሳክ ፱ ነው ፤ ፱ና ፲፭ት ፹፬ት ይሆናል ጾመ አይሁድ ቢወርድ ከመስከረም ፹፬ ቀን ወደ ፹ቦት አይወርድም ወደላይ ሲወጣም ፲፫ት መጥቅዕና ፱ኝ ተውሳክ ፹፪ት ይሆናል ቢወጣ ከጥቅ ምት ፹፪ት ወደ ፹፫ት አይወጣም መመላለሻው ከመስ ከረም ፯ት ከጥቅምት ፹፪ት ፹፱ኝ ይሆናል በዚህ ሲመ ላለስ ይኖራል ።

፪ኛ የበዓለ መጸለት ተውሳክ ፲፬ት ፲፭ና ፲፬ት ፹፱ ይሆናል ። መጸለት ከመስከረም ፹፱ ቀን ወደ ፹፮ አይወርድም ። ሲወጣም ፲፫ና ፲፬ ፹፯ ይሆናል ። ከጥ ቅምት ፹፯ ቀን ወደ ፹፮ ቀን አይወጣም ። መመላ ለሻው ከመስከረም ፱ ቀን ከጥቅምት ፹፯ ቀን ፹፱ ቀን ይሆናል በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ።

፫ኛ የበዓለ ፍሥሕ ተውሳክ ፲ ፤ ፲፭ና ፲ ፹፭ ይሆ ናል ፍሥሐ አሪት ከመጋቢት ፹፭ ቀን ወደ ፹፱ አይወ ርድም ። ሲወጣም ፲፫ና ፲ ፤ ፹፫ ይሆናል ። ከሚያዝያ ፹፫ ቀን ወደ ፹፱ አይወጣም መመላለሻው ከመጋቢት ፮ ቀን ከሚያዝያ ፹፫ ቀን ፹፱ ይሆናል በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ።

መጥቅዕ ከቅዱስ ድሜጥሮስ በፊት በኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ሲሠራበት የቈየ መሆኑን በዚህ ልንረዳ እ ችላልን . . . ለምሳሌ የ፲፱፻፺፮ ዓ. ም. ፍሥሐ አሪት የሚ

www.ethiopianorthodox.org

ውልበትን ቀን ፣ እናሳያለን ፍሥሐ አረት ከሆሣዕና እስከ ቅዳሜ ሥዑር ባሉት ዕለታት ውስጥ ይውላል እንጂ ከሌላ አይውልም ፤ ይኸውም ሆሣዕናና ትንሣኤ የዘመነ ሐዲስ በዓላት ። ስለ ሆኑ ድሜጥሮስ በ ሳሰነው መሠረት በመጥ ቅዕና በተውሳክ ዕለት (የቀን ተጨማሪ ማለት ነው) ይቈጠ ራሉ ፤ ፭ኛ መጽሐፍ ገጽ ፲፯ ላይ ተመልከት ፤ ፍሥሐ አሪት ግን የጥንታውያን ቀኖተር ስለ ሆነ በመጥቅዕ ብቻ ይቈጠ ራል፤የ፲፱፻፶፯ ዓ ም መጥቅዕ ፲፫ ነው፤ ፲፫ና ፲ ፳፫ ይሆናል፤ ፍሥሐ አሪት ሚያዝያ ፳፫ ቀን የስቅለተ ቀን ይውላልና እናስተውል ።

ማሰሰቢያ መስከረም ቅዳሜ ሲጠት መጥቅዕ ፲፫ ሲሆን ነው፤ በላይኛው የመጨረሻ ቀናቸው የሚሉሉ እንደዚሁም መስከረም ዓርብ ሲጠት መጥቅዕ ፲፭ ሲሆን ነው ፤ በታች ኛው የመጨረሻ ቀናቸው የሚሉሉ ስለሆነ እንዳትሰሳቱ አስተውሉ ።

አሁን ወደተነሣንበት እንመለስ ።

፬ኛ. የልበ ምድር ተውሳክ ፫ ነው ፤ ፲፭ና ፫ ፲፰ ይሆ ናል፤ ልበ ምድር ከሚያዝያ ፲፰ ወደ ፲፯ አይወርድም፤ ሲወ ጣም ፲፫ና ፫ ፲፯ ይሆናል ፤ ቢወጣ ከግንቦት ፲፯ ቀን ወደ ፲፯ ቀን አይወጣም ፤ መመላለሻው ከሚያዝያ ፲፫ ቀን ከግ ንቦት ፲፯ ቀን ፷፱ ይሆናል ፤ በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ።

፭ኛ. የበዓለ ሰዊት ተውሳክ ፴ ነው፤ ፲፭ና ፴ ፵፭ ይሆናል፤ ፴ውን ትቶ ፲፭ ይቀራል በዓለ ሰዊት ሲወርድ ከግንቦት ፲፭ ቀን ወደ ፲፱ አይወርድም፤ ሲወጣም ፲፫ና ፴ ፵፫ ይሆናል፤ ፴

ውን ትቶ ፲፫ ይቀራል፤ከሰኔ ፲፫ ቀን ወደ ፲፱ ቀን አይወጣም መመላለሻው ከግንቦት ፲፯ ቀን ከሰኔ ፲፫ ቀን ፷፱ ይሆናል መመላለሻው ይህ ነው ።

፮ኛ ፤ የጾመ አስቴር ተውሳክ ፭፩ ነው ፲፭ና ፷፩ ፴፯ ይሆናል ፤ ፴ውን ትቶ ፯ ይቀራል ፤ ሲወርድ ከነሐሴ ፯ ቀን ወደ ፭ ቀን አይወርድም ሲወጣም ፲፫ና ፭፩ ፴፱ ይሆናል ፤ ፴ውን ትቶ ፱ ይቀራል ፤ ጾመ አስ ቴር ከጳጉሜን ፱ ቀን ወደ ፭ ቀን አይወጣም፤ መመላለሻው ከነሐሴ ፭፭ ቀን ከጳጉሜን ፱ ቀን ፷፱ ይሆናል፤ በዚህ ሲመ ላለስ ይኖራል ።

፯ኛ ፤ የጾመ ዮዲት ተውሳክ ፭፰ ነው ። ፲፭ና ፷፰ ፵፫ ይሆናል ፤ ፴ውን ትቶ ፲፫ ይቀራል ፤ ሲወርድ ከነሐሴ ፲፫ ቀን ወደ ፲፱ ቀን አይወርድም ፤ ሲወጣም ፲፫ና ፷፰ ፵፩ ይሆናል ፴ውን ትቶ ፲፩ ይቀራል ጾመ ዮዲት ከመስከረም ፯ ቀን ወደ ፯ ቀን አይወጣም ፤ መመላለሻው ከነሐሴ ፲፰ ቀን ከጳጉሜን ፭ ቀን ከመስከረም ፯ ቀን ፷፱ ቀን ይሆናል ፤ በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ፤ የበዓላተ አሪት መመላለሻ ፷፱ ቀን ነበር ።

የበዓላተ ወንጌል ግን ተሻሽሎ መመላለሻቸው ፴፭ ቀን ሆኑዋል ፱ኛው መጽሐፍ ገጽ ፯ ተመ፤ ይህ የማሻሻል መሠረት ነው እንጂ በአባቶቻችን ኢትዮጵያውያን ያል ነበረ አዲስ ትምህርት እንዳይመስላችሁ ። እውቀቱ የጥ ንታውያን አባቶቻችሁ ነውና አስተውሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

፯ ተኛ ክፍል ።

ስለ ፯ኛዪቱ ጳጉሜን ሁኔታ በ፫ተኛው ክፍል እን ደገለጽነው ከዚህ ሁኔታውን በዝርዝር እንገልጻለን ። ፭ቱ ዕለታት ጳጉሜንና በ፬ት ዓመት ውስጥ የምትገኝ ውን ፯ኛዪቱ ጳጉሜን በቀን ከሚገኘው ፶፪ ክልኢት ነው የሚገኙ ብለን አስረድተናል ። ስለ፭ቱ ጳጉሜን በ፫ተኛው ክፍል ተጣርቷል ። ስለ ፯ኛዪቱ ጳጉሜን ብቻ እናጣራለን ፣ ይኸውም በአሁኑ ዘመን ማለት ከ፲ ፱፻፺፯ ፣ ዓ. ም. ጀምረን እስከ ፲፱፻፺፱ ፣ ዓ. ም. ድረስ እን ዴት ሁኖ እንደሚቈጠር እንገልጻለን ።

፭ኛ ንኡስ ክፍል።

፭ኛ. መስከረም ፭ቀን የሚውለው ፲፪ት ሰዓት ፣ ፪ት ክል ኢት ፴ ሣልሲት ነው እስከ ወር ቢቆጥሩ ፴ ቀንና ፣ ፭ድ ኬክሮስ ከ፲፭ ክልኢት ነው ።

፪ኛ. በጥቅምት ወር እንደዚሁ ፴ ቀንና ፭ድ ኬክ ሮስ ከ፲፭ ክልኢት ነው ።

፫ኛ. በኅዳር ወር እንደዚሁ ፴ ቀንና ፭ድ ኬክ ሮስ ፲፭ ክልኢት ነው ።

፬ኛ. በታኅሣሥ ወር እንደዚሁ ፴ቀንና ፭ድ ኬክሮስ ከ፲፭ ክልኢት ነው ።

በታኅሣሥ ፴ቀን ፬ት ወር ከ፭ት ኬክሮስ ይሆናል ፣ (ማለት ፬ት ወር ከ፭ድ ሰዓት ነው ።

፪ኛ ንኡስ ክፍል ።

ከጥር ፭ድ ቀን እስከ ሚያዝያ ፴ ቀን ፬ ወር ከ፭ት ኬክሮስ ነው ።

፫ኛ ንኡስ ክፍል ።

ከግንቦት ፩ ቀን እስከ ነሐሴ ፴ ቀን ፬ት ወር ከ፭ት ኬክሮስ ነው ። ኬክሮስ ማለት በዛፊው ፲፪ ይቂቃ ነው ። በ፲፪ ወር ፫ ሰዓት አለፈ ፣ ተሠርቶበታል ማለት ነው ። በአሁኑ ዘመን ዮሐንስ ፫ቱ ሰዓት ተሠርቶበት አለፈ ፩ ቀን ጳጉሜን ክክልኢት የተገኘ ስለሆነ ኬክሮስና ክልኢት የለውም ከ፲፪ቱ ወር ብቻ ነው የሚቈጠረው አስተውሉ ።

፪ኛ. በዘመነ ማቴዎስ ፶፯ ዓ. ም. እንደዚሁ ፫ቱ ሰዓት ተሠርቶበት ያልፋል ።

፫ኛ በዘመነ ማርቆስ ፶፰ ዓ. ም. እንደዚሁም ፫ቱ ሰዓት ተሠርቶበት ያልፋል ።

፬ኛ በዘመነ ሉቃስ ፶፱ ዓ. ም. ፫ቱ ሰዓት ተሠር ቶበት ያልፋል ። በ፲፱፻፺፱ ዓ. ም. በዘመነ ሉቃስ የ፯ ኛይቱ ጳጉሜን ቍጥር በነሐሴ ፴ ቀን ሙሉ ፲፪ ሰዓት ይሆናል ። ነገር ግን የነሐሴ ወር በ፬ኛው ዓመት ፴፩ ቀን መሆን ሲገባው የጥር፰ም ቍጥር ስለሆነ ከ፭ት ቀን ጳጉሜን በኋላ ፯ና ቀን እንድትሆን ተደርጓል ከዚህ ውስጥ ያለ ማሻሻል ማስተዋል በቂ ይሆናል

ስለ በዓለ ልደት የ፲፱፻፺፰ ዓ. ም. በ፳፰ ቀን ታኅ ሣሥ ስለሚከበር ከዚሁ አቈጣጠር የሄድን እንደሆን

www.ethiopianorthodox.org

የ፲፱፻፷፫ ዓ. ም. ቍጥር በታኅሣሥ ፴ ቀን ትርፍ ፩ ሰዓት ስለሚገኝ ይህ ትርፍ ቍጥር የሚያገለግለው እስከ ፬ ዓመት ቄይቶ ነው እንጂ በተሠራበት ቀን አይቈጠርም ። ምክንያቱም በማሻሻል ተስማምተው ስለ ወሰኑት ነው ።

የኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የሰዓት ቍጥር

፩ኛ፦ በፊቱ ጸጉሜን ሰዓት ቈጣሪው ከክሮስ ተመድቧል።

፪ኛ፦ በ፴፩ ቀን ደቂቃ ቈጣሪው ከንትሮስ ተመድቧል ።

፫ኛ፦ በ፬ ወር (ማለት በ፮ ቀን) የሙሉ ቀን ቈጣሪ ተመድቧል ።

፩ኛ ከክሮስ ፩ ሰዓት ነው ። ፴ ከንትሮስም ፩ ሰዓት ነው ።

ከልኢትና ሣልሲትም ከከንትሮሱ ቍጥር ይታሰባሉ ።

፮ ከክሮስ ፲፪ ሰዓት ነው ። ፩ኛ ፲፪ ደቂቃ ነው ፤ በድሮው ዘመን ግን ፮ ደቂቃ ነው ። 5 × 6 :-30 ይሆናል። ፩ × ፮ ÷ ፴ ይሆናል ። በዛሬው ግን ፯ ደቃቃ ነው ። የቀድሞ አባቶች ቍጥር ይርብ ነው ። የዛሬው ግን ዝርዝር ነው ።

፮ቱ ፲፪ ፴ው ፮ ብለን መግለጻችን ጠጣቱ ትውልድ አውቆ እንዲሠራበት በማሰብ ነው ።

፮ኛ ክፍል ።

ስለ ፀሐይ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ መጓዝ (ጥንታዊው ሳይንስ) ፀሐይ ስአባቶቻችን በተገኘው እውቀት ዘወትር ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የምትጓዝበትን ሁኔታ

አስረድተው ጽፈዋል ይኸውም ከዚህ ቀጥሎ ያለው ጽሑፍ በአጭሩ ያስረዳናል ።

ሠረገላ ፀሐይ እንደምን ነው ቢሉ አውታረ ፀሐይ ፱ሺሕ ከ፱፪ ነው (ሠረገላ መሄጃ መሆኑ ግልጽ ነው) ከ፱ሺሕ ፱፪ አውታር ፯ሺህ ከ፯፪ አውታር እንደ ዘሐ ከምሥራቅ እስከ ምዕራብ የተነጸፈ ነው (የተዘረጋ ነው) ፫ሺሕ ከ፫፪ው አውታር ደግሞ ከሰሜን እስከ ደቡብ እንደ ግራ (እንደ ማግ) የተዘረጋ ነው ።

እንደዚሁም ምሕዋረ ፀሐይ (የፀሐይ መንገድ) ፱፻፲ ነው ። አእጋረ ፀሐይ ፫፻፷ ነው ። ምዕዛረ ፀሐይ ፻፷ ነው ።

መስኩቶችዋ ፯ት በምሥራቅ (የፀሐይ መውጫ) ፯ት በምዕራብ (የፀሐይ መግቢያ) ነው ብለው አባቶቻችን ኢትዮጵያውያን በብዕትም በትምህርትም የደረጁ ስለሆኑ ፀሐይ የምትጓዝ መሆኗን በእርግጥ አስረድተዋል ።

የዛሬው እውቀት ግን ፀሐይ አትንቀሳቀስም ። የምትዘረው መሬት ናት የሚል ትምህርት ዘርግቷል ። በተመልክቶች ዘንድ ግን እንደ ጥንታውያኑ እውቀት ፀሐይ የምትጓዝ መሆኗን ሊያምንበት የሚያስችል የቅርብና በየጊዜው የሚታይ አስረጅ አለን ። ይኸውም በየአንዳንዱ ሰው ቤት ያልሠራ የለም ፤ ቤቱም በምሥራቅና በምዕራብ መስኩቶች አሉት በጥዋት መስኩቱ ሲከፈት ገና ፀሐይ ስትወጣ ብርሃኗ በትክክል በመስኩቱ ገብቶ በመ

www.ethiopianorthodox.org

ጨረሻው ወደ ምዕራብ ባለው ግድግዳ ላይ ያርፋል ። ፀሐይ በጥቂት ጉዞዋን ወደላይ ስትቀጥል ወደ ቤቱ ገብቶ የነበረው ጮራ ጫልጥ ብሎ ዓይናችን እያየ ወጥቶ ይሄዳል ።

እንዲያውም ፀሐዩ አርፎበት የነበረውን የቤቱ ግርግዳ (ወይም ግንብ) ፀሐዩ ለቆ ጥላ ያርፍበታል ። በ፮ ሰዓትም ፀሐይ በትክክል ወደላይ ስለ ወጣች ብርሃኗ ወይም ጮራዋ በቤቱ ጣራ ባለው ቀዳዳ ትክክል ገብቶ ከምድር ቤቱ ላይ አርፎ እናየዋለን ። በ፯ ሰዓትም ብምዕራብ ጥላ አርፎበት የዋለውን ግድግዳ ፀሐይ ያርፍበታል ፤ ጥላውን ያስወገደ የፀሐይ ጉዞ አልፎ በመገኘቱ ነው ። እንዲያውም የምዕራቡ መስኮት ሲከፈት እንደጥዋቱ የፀሐዩ ጮራ ብመስኮቱ ገብቶ በምሥራቅ ወዳለው ግድግዳ ላይ አርፎ እናየዋለን ። በዚህ ጊዜ ይህ ሁኔታ የፀሐይ መጓዝ ምልክት ነውን ? ወይስ የመሬት መዞር ምልክት ነው ? ብለን ብንጠይቅ የገዛ ሕሊናችን ጉዞው የፀሐይ ነው የሚል መልስ ይሰጠናል ። ይህ ምልክት የመሬት መዞር አይደለም ፤ በበኩሌ ስለዚህ የኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ምርመራ እርግጠኛ ነው እላለሁ ።

እንደዚሁም ዓለም የተፈጠረበት ቀን ከአዳም ወዲህ አይደለም ቀድሞ የነበረ ነው ልኩ አያታወቅም የሚሉ መምህራን መኖራቸውን እንሰማለን ። ይህም ከኢትዮጵያውያን አባቶቻችን እውቀት የተሠወረ አይደለም ። ይህም ይታወቅ ዘንድ ይህ ዓለም በመጋቢት ፳፱ ቀን እሁድ ተፈጠረ ብለው አስተምረው ጽፈዋል ። በዚህ ጊዜ ፳፰ ቀን ወደ ኋላ መኖሩን ገልጸዋል ። ነገር ግን ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን በእውቀትም በቅድስናም የተጠበቁ ስለሆነ መብቱም ስለማይፈቅድላቸው እንደሌሎቹ ነው ብለው ለማስተማር አልፈቀዱም ። ከዚያ በፊትሳ ምን ነበር ብሎ ለሚጠይቃቸውም ፤ ፈጣሪ ራሱ ባወቀ ነው እንጂ እኛ እናውቅም የሚል መልስ ይሰጣሉ ፤ ከዚህ ያለፈ ነገር ነበረ አልነበረም የሚል ድምዕ አልተሰማባቸውምና ።

ይህ የአባቶቻችን እውቀትና ቅድስና ሊጠበቅ ይገባዋል እላለሁ ። ዓለም አያልፍም የሚሉ መምህራንም መኖራቸውን እንሰማለን ። ይህም ከኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የተሠወረ አይደለም ። ምክንያቱም በ፱ኛው ክፍል ተመልክት ።

፱ኛ ክፍል ።

በጥንታዊው አቈጣጠር ሁሉም በ፴ በ፴ ነው ያልንበትን ሁኔታ ከዚህ በተለይ አብራርተን እንገልጻለን ። ፩ኛ ፩ድ ክልኢት ፫ ሰከንድ ነው ።

፪ኛ ፩ድ ከንትሮስ ፩ድ ደቂቃ ነው ። (በ፱ኛው ክፍል ከዘመናዊው ጋር በማገናኘት ተጽፏል ፤ አሁን ግን በተለይ ነውና እናስተውል ።)

፫ኛ ፩ድ ኬክሮስ ፯ ደቂቃ ነው ። ፬ኛ ፭ት ኬክሮስ ፩ድ ሰዓት ነው ፭ኛ ፲ ክልኢት ፩ ከንትሮስ ነው ፮ኛ ፯ ከንትሮስ ፩ድ ኬክሮስ ነው ። ፯ኛ ፭ ኬክሮስ ፩ ሰዓት ነው ።

ወረ ብለው አስተምረው ጽፈዋል ። በዚህ ጊዜ ፳፰ ቀን ወደ ኋላ መኖሩን ገልጸዋል ። ነገር ግን ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን በእውቀትም በቅድስናም የተጠበቁ ስለሆነ መብቱም ስለማይፈቅድላቸው እንደሌሎቹ ነው ብለው ለማስተማር አልፈቀዱም ። ከዚያ በፊትሳ ምን ነበር ብሎ ለሚጠይቃቸውም ፤ ፈጣሪ ራሱ ባወቀ ነው እንጂ እኛ እናውቅም የሚል መልስ ይሰጣሉ ፤ ከዚህ ያለፈ ነገር ነበረ አልነበረም የሚል ድምዕ አልተሰማባቸውምና ።

ይህ የአባቶቻችን እውቀትና ቅድስና ሊጠበቅ ይገባዋል እላለሁ ። ዓለም አያልፍም የሚሉ መምህራንም መኖራቸውን እንሰማለን ። ይህም ከኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የተሠወረ አይደለም ። ምክንያቱም በ፱ኛው ክፍል ተመልክት ።

፱ኛ ክፍል ።

በጥንታዊው አቈጣጠር ሁሉም በ፴ በ፴ ነው ያልንበትን ሁኔታ ከዚህ በተለይ አብራርተን እንገልጻለን ። ፩ኛ ፩ድ ክልኢት ፫ ሰከንድ ነው ።

፪ኛ ፩ድ ከንትሮስ ፩ድ ደቂቃ ነው ። (በ፱ኛው ክፍል ከዘመናዊው ጋር በማገናኘት ተጽፏል ፤ አሁን ግን በተለይ ነውና እናስተውል ።)

፫ኛ ፩ድ ኬክሮስ ፯ ደቂቃ ነው ። ፬ኛ ፭ት ኬክሮስ ፩ድ ሰዓት ነው ፭ኛ ፲ ክልኢት ፩ ከንትሮስ ነው ፮ኛ ፯ ከንትሮስ ፩ድ ኬክሮስ ነው ። ፯ኛ ፭ ኬክሮስ ፩ ሰዓት ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ ቀጥለን በየአንዳንዱ ሁኔታውን ይቀጥላል ።
፩ኛ· ፲ ክልኢት በ፫ ሰከንድ ሲበዛ ፲×፫= ፴ ይሆናል ፤
፴ ሰከንድ ፩ሮ ከንትሮስ (ወይም ፩ድ ደቂቃ) ይሆናል።

፪ኛ· ፯ ክንትሮስ ሲበዛ ፯ + ፭ =፲፪ ይሆናል ።
፫ኛ· ፭ ኬክሮስ ሲበዛ = ፭ + ፯=፲፪ ይሆናል ።
፭ ኬክሮስ ፲፪ ክንትሮስ (ወይም) ፲፪ ደቂቃ ነው ።
፩ ክንትሮስ ፲ ክልኢት (ወይም ፲፪ ሰከንዮ) ነው ።
፭ ኬክሮስ ፲፪ ክንትሮስ (ወይም ፩ ሰዓት(ነው ።

በእውኑ ሥልጠኔ ግን ፤

፩ ኬክሮስ ፲፪ ደቂቃ ነው ። . . ፲፪ ክንትሮስም ፭ ደቂቃ ነው ። . . . ፲ ክልኢትም ፭ ሰክንድ ነው ። . . . ፩ ክልኢት ፯ት ሰክንድ ሆነ ማለት ነው ። ፩ዱም ክንትሮስ ፲፪ ደቂቃ ሆነ ማለት ነው ። (ክልኢት ማለት ፯+ ፲=፭ ይሆናል ።) ክንትሮስ ፲፪+ ፲፪=፭ ይሆናል ።) ፩ዱ ኬክሮስም ፲፪ ደቂቃ ሆነ ማለት ነው

፭×፲፪ =፭ ደቂቃ ሆነ ። ከዚህ ቀጥዬ ወጣቱ ትውልድ እንዲያስፋፋውና እንዲሠራበት አስረክቤ አለሁ ።

፲ኛ ክፍል

ጥያቄ በዓላትና አጽዋማት በ፴፭ ቀን እየተዘዋወሩ እንዲውሉ ያደረገ ማነው ጴጥሮስ ነውን ? ማርቆስ ነውን? ድሜጥሮስ ነውን ? ለይተህ አስረዳኝ ?

መልስ. በዓላትንና አጽዋማትን በ፴፭ ቀን እየተዘዋወሩ እንዲውሉ ያደረገ ቅዱስ ድሜጥሮስ ነው ።

ጥያቄ. ከእርሱ በፊትስ በምን ቀን ይውሉ ነበር ፤ አስረዳኝ ? (መልስ) ሰኞም ማክሰኞም ባልተወሰነ ቀን ይውሉ ነበር ።

(ጥያቄ) ባልተወሰነ ቀን ሲውሉ ጥንተ መሠረታቸውን ለቀው ነውን ? ወይስ ሳይለቁ ነው ?

(መልስ) ጥንተ መሠረታቸውን ሳይልቁ ነው ።

(ጥያቄ) መሠረታቸውን ለቀው እንዲውሉ ያደረገበት ምክንያት ምንድር ነው ።

(መልስ) ትንግኤ ፤ ሆሣዕና ፤ ጰራቅሊጦስ ፤ መሠረታቸው አሐዱ ነበር ፤ ሌሎቹም በዓላት እንደዚሁ በየቀናቸው እንዲከብሩ አስበ በማሻሻል መሠረቱን ለቆ እንዲውል (ወይም እንዲከብር) አደረገ ፤ ምክንያቱ ይህ ነው ።

(ትርፍ) ጥያቄ ሊከበር የሚገባው ሥራው ነውን ። ወይስ ቀኑ ነው ? ።

(መልስ) በእውነቱ ሊከበር የሚገባው ሥራው ነው እንጂ ቀኑ አይደለም ።

(ጥያቄ) በአንድ ወገን መሠረቱ ሲለቅ ፤ በአንድ ወገን ደግሞ ባልተሠራበት ወራት ተሠራበት ብሎ ማክበር ስሕተት አይሆንም ወይ ።

መልስ በማሻሻልና ዘመስማማት የተወሰነ ስለሆነ ስሕተት አይሆንም ።

(መጀመሪያው ጥያቄ)

www.ethiopianorthodox.org

ጥያቄ. ጌቱ ቀን ጻጉሜን በዓመት በዓመት የሚገኙ እንዲሁም በ፬ ዓመት በ፬ ዓመት የምትገኝ ጄኛዪቱ ጻጉሜን ከምን የተገኙ ናቸው አስረዳኝ ።

መልስ አባቶቻችን ኢትዮጵያውያን እናዳስረዱን ከዓ የር ምርመራ ፀሐይ ከጨረቃ በልጣ ከምታበራው ታስበ የተገኘ ነው ።

ጥያቄ. የአየር ምርመራና የፀሐይ ብልጫ ያስገኘው ይህ ብቻ ነውን ? ወይስ ሌላ አለ ? ለይተህ አስረዳኝ ?

መልስ ፭ኛ ከ፭ ኬክሮስ የተገኘ ጄት ሕፀፅ አለ፣ ፭ኛ ከ፭ ግልሲት በጄ፱ ጓመት መጨረሻ የምትገኝ ሄና ጻጉሜን አላች ይላሉ ።

ጥያቄ. አለች የተባለችው ፭ኛ ጻጉሜን እንደ ጌቱ ጻጉሜን ከዓመት አግብተው ቁጥረዋታልን ? ወይስ አል ቈጠሯትም አስረዳኝ ?

መልስ. ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የእውቀት ደረ ጃቸውን ለመግለጽ አለች ብለው የምትገኝበትን ሁኔታ አብራርተው ጻፉ እንጂ ከዓመት አግብተው አልቈጠሯ ትም ።

ጥያቄ. የጄኛዪቱ ጻጉሜን ቀኖጥር ታውቋል ከዓ መት አግብተው አይቀጠሯት እንጂ በአሷ ቀኖጥር ከልደተ ክርስቶስ ፀሬትና ከልደተ ክርስቶስ ወዲህ እስከ ዛሬ (ማለት እስከ ፲፱፻፺፯ ዓ ም) ስንት ቀን እንደሆነች ለይተህ አስረዳኝ ።

መልስ ከቀኖጥር አልገባችም እንጂ ከልደተ ክርስቶስ በፊት ፱ ቀን ከ፲ ኬክሮስ ውና ነበር፣ ከልደተ ክርስቶስ ወዲህም ማለት እስከ ፲፱፻፺፯ ዓ ም ፫ ቀን ከ፲፭ ኬክሮስና ከ፴፯ ክልኢት ውናለች ። በጠቅላላው ፲፪ ቀን ከሜ፩ ኬክሮስ ከ፴፯ ክልኢት ውናለች ማለት ነው ።

ጥያቄ ፣ በጥንቱ አነጋገር ኬክሮስ ማለት ምን ማለት ነው ?

መልስ. የሰዓት ቈጣሪ ማለት ነው ።

ጥያቄ ከንትሮስ ማለትስ ምን ማለት ነው ?

መልስ. የደቂቃ ቈጣሪ ማለት ነው ።

ጥያቄ. ክልኢት ማለትስ ምን ማለት ነው ?

መልስ. ሰከንድ ማለት ነው ።

ጥያቄ. ግልሲት ማለትስ ምንድር ነው አስረዳኝ ?

መልስ የሰከንድ ሰከንድ ማለት ነው ።

፲፩ኛ ክፍል ።

ጥያቄ. ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን የሚሰብ እውቀት የተማሩት ከቅዱስ ድሜጥሮስ ነውን ? ወይስ ከእርሱ በፊት አዋቂዎች ኑረዋል ።

መልስ. ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን እውቀታቸው ከጥንት ነው እንጂ የድሜጥሮስ ብቻ አይደለም ።

ጥያቄ በዘመነ ብሉይ ኢትዮጵያውያን የበዓላትና የአጽዋማት ቀኖጥር (ማለት የሚሣብ መጽሐፍ) ነበራቸውን ?

መልስ በሚገባ የበዓላትና የአጽዋማት ቀኖጥር የተጠናቀቀ እውቀትና መጽሐፍ ነበራቸው ፣ አሁንም አለ ።

www.ethiopianorthodox.org

ጥያቄ፦ የበዓላተ አሪትና የአጽዋማተ አሪት የቀኖተ
ውቸ መነሻና መድረሻ ምን ይባላል ?

መልስ፦ የቀኖተራቸው መነሻ መጥቅዕ መድረሻው
ተውሳክ ይባላል ።

ጥያቄ፦ ተውሳክ ማለትና መጥቀዕ ማለት ምንድ
ነው ።

መልስ፦ መጥቅዕ ማለት ደወል ወይም ነጋሪት ነው ።
ተውሳክ ማለትም ተጨማሪ ማለት ነው ።

ጥያቄ የቀኖተር መነሻ ሲሆን ለምን መጥቅዕ ተባለ

መልስ፦ ደወልና ነጋሪት በተመቱ ጊዜ ተፈላጊው
ሕዝብ እንዲሰበሰብ ይህም መጥቅ ተፈላጊዎቹን በዓላት
ንና አጽዋማትን በማስገንዘቱ ነው ።

ጥያቄ፦ በዓላተ አሪት እንደ በዓላተ ወንጌል በመጥቅ
በተውሳክ ዕለት እንዲሁም በየተውሳክቸው ተጨምሮ
ይቄጠራሉን ? ወይስ ልዩነት አላቸው ለይተህ አስረዳኝ ።

መልስ፦ በዓላተ አሪት እንደ በዓላተ ወንጌል ቁጥር
ተውሳክ ዕለት የላቸውም በመጥቅና በተውሳክቸው ብቻ
ይቆጠራሉ ።

ጥያቄ በዓላተ አሪት ወደላይ ሲወጡ የሚውሉበት
ቀንና ወደታች ሲወርዱ የሚውሉበት ቀን (ማለት ኢየሳ
ርጉ ኢይወርዱ) ማመላለሻቸውን እንደ በዓላተ ወንጌል
የተወሰነ ነውን ? ወይስ ውሳኔ የለውም አስረዳኝ ።

መልስ የተወሰነ መመላለሻ ፸፱ ቀን አላቸው ።

ጥያቄ የበዓላተ ወንጌልስ መመላለሻቸው ስንት
ቀን ነው ?

መልስ የበዓላተ ወንጌል መመላለሻ ፴፭ ቀን ነው ።

ጥያቄ ይህ ልዩነት የፈጠረበት ምክንያት ምንድ
ነው ተጨማሪውስ ስንት ነው

መልስ በሐዲስ ዘመን ቅዱስ ድሜጥሮስና በዘመኑ
የነበሩ ሊቃውት ተስማምተው በማሻሻል ከመጥቅዕ ጋራ
የሚቈጠር ተውሳክ ዕለት ስለጨመሩ የበዓላተ ወንጌልን
መመላለሻ ፯ት ቀን ጨምረው በ፴፭ ቀን እንዲመላ
ለሱ ስለ ወሰኑ ነው ።

ጥያቄ በማሻሻል የተወሰነ ሁሉ ይጠቅማልን

መልስ እንደ ጥንታውያን አባቶቻችን ሳይነቃቀፉ
በማሻሻል የተወሰነ ሁሉ ይጠቅማል ።

፲፪ኛ ክፍል ።

ጥያቄ በዓላተ አሪትና በዓላተ ወንጌል ወደላይ ሲወ
ጡና ወደታች ሲወርዱ የሚታወቅበት ውሳኔ አለን ወይስ
የለም ለይተህ አስረዳኝ ።

መልስ የተወሰነ አለ ። ይኸውም ወደታች የሚወር
ርዱበት መጨረሻ መጥቅዕ ፲፭ ሲሆን መስከረም ዓርብ
ሲብት በዓለ ሙጥቅዕ መስከረም ፲፭ ቀን ዓርብ ሲውል
በታችኛው የመጨረሻ ቀናቸው ይውላሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወደላይ የሚወጡበትም መጨረሻ ቀን መጥ
፲፫ ሲሆን መስከረም ቅዳሜ ሲብት በዓለ መጥቅዕ ጥቅ
ምት ፲፫ ቀን ቅዳሜ ሲውል በላይኛው የመጨረሻ ቀና
ቸው ይውላሉ ። ውሳኔያቸው ይህ ነው ።

ጥያቄ ፭ኛ መጥቅዕ ፲፭ ሁኖ መስከረም ከእሁድ
እስከ ሐሙስ ሲብት በዓለ መጥቅዕም በነዚሁ ቀን ሲውል
ወደታችኛው የመጨረሻ ቀናቸው ይወርዳሉን ? ፪ኛ
እንደዚሁም መጥቅዕ ፲፫ ሁኖ መስከረም ከእሁድ እስከ
ሐሙስ ሲብት በዓለ መጥቅዕ ጥቅምት በነዚሁ ቀኖች
ሲውል ወደ ላይኛው የመጨረሻ ቀናቸው ይወጣሉን ?
ለይተህ አስረዳኝ

መልስ በ፲፭ መጥቅዕ ጊዜ በዓላቱ አሪት ወደታች
ኛው የመጨረሻ ቀናቸው አይወርዱም እንጂ በተወሰነ
ላቸው ፳፱ ቀን ውስጥ ወደ ታችኛው ይውላሉ ። እንደ
ዚሁም በዓላተ ወንጌል በተወሰነላቸው ፴፭ ቀን ውስጥ
ወደታችኛው ይውላሉ ። በ፲፫ መጥቅዕ ጊዜም በዓላት
አሪትና በዓላተ ወንጌል ወደ ላይኛው የመጨረሻ ቀና
ቸው አይወጡም እንጂ በተወሰነላቸው በዓላተ አሪት
በ፳፱ ቀን ውስጥ ፣ በዓለተ ወንጌል በ፴፭ ቀን ውስጥ
ወደላይኛው ቀናቸው ይውላሉ ።

ጥያቄ የ፯ኛዬቱ ጳጉሜን ቍጥር በ፬ት ዓመት መጨ
ረሻ የምትውልበትን ሁኔታ ዘርዝረህ አስረዳኝ ?

መልስ በአሁኑ እንጀምር ግለት በ፲፱፻፺፮ ዓ. ም.
መስከረም ፴ ቀን ፭ድ ኬክሮስ ከ፲፩ ክልኢት ያልፋል

በዚሁ ቍጥር እስከ ታኅሣሥ ፴ ቀን ፭ ኬክሮስ ይሆናል ።
፭ ኬክሮስም ፭ ሰዓት ነው ፤ በ፲፱ኛው ወር ነሐሴ ፴ ቀን
፲፭ ኬክሮስ ይሆናል ፲፭ ኬክሮስም ፫ ሰዓት ነው ይህ
፫ ሰዓት በዘመነ ዮሐንስ ተሠርቶበት አልፏል በዚሁ አቈ
ጣጠር በ፲፱፻፺፬ ዓ ም በዘመነ ሉቃስ ነሐሴ ፴ ቀን ፲፱
ሰዓት ይሞላል ፤ በዓመት በዓመቱ ፫ት ፫ት ሰዓት ተሠርቶ
በት ያለፈ ነው ።

ጥያቄ በዓመት በዓመቱ ፫ ሰዓት ተሠርቶበት ያለፈ
ከሆነ ለምን በ፬ኛው ዓመት ፮ተኛ ጳጉሜን ተብሎ ተቈ
ጠረ ።

መልስ አባቶቻችን ተስማምተው የወሰኑት ስለሆነ
ተሰብስበ በ፬ኛው ዓመት ፩ ቀን ተብሎ ተቈጠረ ።

፲፫ኛ ክፍል ።

ጥያቄ ጥንታውያን አባቶችኅን ፀሐይ ትጓዛለች ይላሉ ።
የዛሬው ትውልድ ደግሞ መሬት ትዞራለች እንጂ ፀሐይ
አትንቀሳቀስም ይላል ፤ እንተስ ምን ይመስልሃል ?

መልስ ፀሐይ ጥዋት ከምሥራቅ ስትወጣ ማታም
ወደ ምዕራብ ስትገባ በዓይኔ እያየሁ ክዚሁም ላይ የቤታ
ችን መስኮትና ያረፍኩበትን የማንኛውም ጥላ በትንሽ
ደቂቃዎች ውስጥ በፀሐይ መጓዝ ምክንያት ሲዘዋወር እያ
የሁ ይህ ሁኔታ የመሬት መዞር ነው እንዲህ ያደረገው
አልልም በበኩሌ እንደ አባቶቻችን ጉዞው የፀሐይ ነው
እላለሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

ጥያቄ ኢትዮጵያውያን አባቶቻችን ጉዞውን ለፀሐይ ይስጡ እንጂ በምሥራቅ ፮ት መስከት በምዕራብ ፮ት መስከት የፀሐይና የጨረቃ በር መኖሩን ገልጸዋል ። እንደዚሁም በ፲፱ በ፲፱ ዓመት እየዘሩ በ፩ኛው በር የሚገኙ መሆናቸውን በጉልህ አስረድተዋል ። በዚህ ጊዜ ፀሐይና ጨረቃ ናቸውን መንገዳቸውን እየለቀቁ የሚዘሩት ወይስ በሮቹን የያዘች መሬት ናትን የምትዘረው በበኩልህ የዚህ ሁኔታ ምን ይመስልኻል ።

መልስ ፤ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ጥያቄዎች አባቶቻችን በእርግጥ አስረድተዋል ሲያስረዱም ፀሐይና ጨረቃ ዙረው ይገናኛሉ ነው ያሉት ፤ ሁኖም ይህ መሠረቱን ያለቀቀ አስተያየት በበኩሌ የዛሬው ትውልድ እውቀቱን በማሻሻል ወደከፍተኛ እውቀት የደረሰ ስለ ሆነ መሬት ትዘራለች ብሏል እኔም ለአሁኑ ጥያቄ ።

እንደ አሁኑ ትውልድ በሮቹን የያዘች መሬት ትዘር ይሆናል እላለሁ ።

ጥያቄ ዓለም የተፈጠረበት መጋቢት ወር ሲሆን በኢትዮጵያችን የዘመን መለወጫ መስከረም ፩ ቀን የሆነበት ምክንያት ምንድር ነው ።

መልስ በቅዱስ ድሜጥሮስ ሐሳብ በዘመኑ የነበሩ ሊቃውንትና ሕዝብ ተስማምተው በማሻሻል የዘመን መለወጫው መስከረም ፩ድ ቀን እንዲሆን ስለ ወሰኑ ነው እንጂ እንደ አባቶቻችን ቍጥር አጀማመርስ የዘመን መለ

ወጫ መጋቢት መሆን ነበረበት ። ነገር ግን ታውቆ የተወሰነ ስለሆነ ነው ።

ጥያቄ በጥንታውያን አባቶቻችን ሰዓት ሲቈጥሩ የሰዓት ቈጣሪውን ምን ይሉት ነበረ ፫ የደቂቃና የስከንድ ቈጣሪን ምን ይሉት ነበር ።

መልስ የሰዓት ቈጣሪውን ኬክሮስ ይሉት ነበር ፤ የደቂቃ ቈጣሪውን ከንትሮስ የሰከንድ ቈጣሪውን ካልኢት ይሉት ነበር ።

ጥያቄ በጥንቱ አቈጣጠር ኬክሮስ ስንት ደቂቃ እንደሆነ ከንትሮስም ስንት ደቂቃ እንደሆነ ካልኢትም ስንት ስከንድ እንደሆነ ለይተህ አስረዳኝ ።

መልስ ኬክሮስ ፮ ደቂቃ ነው ከንትሮስም ፭ድ ደቂቃ ነው ካልኢትም ፫ ስከንድ ነው ።

ነገር ግን በዛሬው ቍጥር ፱ት ፱ት ይሆናል ፴ ደቂቃ ፭ድ ሰዓት የነበረው ፷ ደቂቃ ማለት ነው ።

ከዚህ ቀጥሎ አስተማሪው በመጽሐፉ ያለ ሁሉ ።

ጥያቄና መልስ እያዘጋጀ ሊያስተምር ይችላል አስጀምሮ ላስፈጸመን አምላክ ክብር ምስጋና ይግባው አሜን ።

ይቀጥላል

www.ethiopianorthodox.org

ማሳሰቢያ ።

፩ኛ ፤ በፊኛው መጽሐፍ በ፱ኛው ክፍል ላይ ከገጽ ፲፫ት ስለ ጥንታዊው ቊጥር አከፋፈል ገርገር የ፭ዱን ክፍል ፲፰፻፺፰ ፤ ብቻ የአከፋፈሉን ሁኔታ ይገልጻል እንጂ ጠቅላላውን የ፱ቱ ክፍል አልተገለጸም ። ፪ኛ ስለ ፯ኛዪቱ ጳጉሜን አቈጣጠር ከገጽ ፸፯ ጀምሮ እንደተዘረዘረው በ፱ት ዓመት ውስጥ ፲፪ ሰዓት ተሠርቶበት ያለፈ መሆኑን ይገልጻል ። ፲፪ቱ ሰዓት በየጊዜው ያለፈ ከሆነ በምን ምክንያት ሌላ ተጨማሪ ፲፪ ሰዓት (ማለት ፩ድ ቀን) ተጨምሮ እንዲቈጠር ተደረገ በማለት ሁለቱ ወጣቶች የጠየቁትን ጥያቄ በማመስገን ሁኔታውን እንገልጻለን ።

፩ኛ እንደ አባቶቻችን ቊጥር ዓለም ከተፈጠረ እስከ ዛሬ ድረስ (ማለት እስከ ፲፱፻፺፯ ዓ፡ ም፡) ፯ ሺህ ፱፻፺፯ ዘመን ሆኖአል የዚህም ንባብ በሮ፻ ወ ፱፻ ፺ወ፯ ዓመተ ዓለም ተብሎ ይነበባል ። (፯ሺህ ፱፻፺፯ ዘመን ማለት ነው) አሁንም ይህኑ እንደ ጥያቄው ከ፱ት ከፍለን እናሳያለን ።

ጠቅላላውን አከፋፈል ።

፲፪ ፳፻፸፰ = ክፍል

ሮ፱፻፺፯ ፡ ፬ ጊዜ (የተከፈለበት)

፵፪
፴፱፻
፴፱፻
፱፻፺
፱፻፺
፲፯
፲፯

ለ፱ቱ ልክ ይደርሰል የተባለውን ሁኔታ

አከፋፈሉ ይህ ነው ። የመጀመሪያው ክፍል ፲፪ (ማለት ፩ሽህ) ሁለተኛ ክፍል ፳፻፸፰ ሦስተኛ ክፍል ፳ አራተኛ ክፍል ፱ት ነው ። አሁን በተሻለ ሁኔታ እናሳያለን (ለየአንዳንዱ ክፍል)

፲፳፻፸፰
፲፳፻፸፰ (ጠቅላላ)

ሮ፱፻፺፯ ፡ ፬ ጊዜ

፵
፴፱፻
፴፱፻
፱፻፺
፱፻፺
፲፯
፲፯

የአንዱ ክፍል አሠርቱ ወሰመንቱ ምዕት ሥሳ ወአርባዕቱ ተብሎ ይነበባል (ሽህ ፳፻፸፰ ማለት ነው) ጠቅላላውም ሲቈጠር ወይም ሲነበብ ዘሰባአ ምዕት ወአርባዕቱ ምእት ሃምሳ ወስድስቱ ዓመተ ዓለም ተብሎ ይነበባል ማለት ነው ።

ባሥልጣኔው ቊጥር አከፋፈል 1864 የአንዱ ክፍል ጠቅላላ ቊጥር 7456 ፡ 4 =

4
34
32
25
24
16
16

www.ethiopianorthodox.org

ስለ ሂሣቡ ሁኔታ ይህ ነው ። ስለ ስድስተኛይቱ ጳጉሜን ግን አባቶቻችን ተስማምተው አንዱን ቀን በ፬ ኛው ዓመት ሁል ጊዜ ጌተኛ ጳጉሜን ይሁን ብለው ስለ ወሰኑ ነው እንጂ ሰዓቱስ በእግዚአብሔር እጅ ስለሆነ በጊዜው ይመራበታል እንጂ ሰብስቦ ለማቄየት ለማንም አይቻለውም ምን ጊዜም በመስማማት የሚሠራ ሁሉ የጸና ነው ።

ከዚህ የበለጠ (ማለት ከመስማማት) ማስረጃ የለምና መስማማትን መሠረት አድርገን እንሥራ ።

መልሱ ይህ ነው ።

ከመምህር ኪዳነ ማርያም ገብረ ሕይወት ተዘጋጅተው የታተሙ መጻሕፍት ።

፩ኛ የዴር ሡልጣንና ጎልጎታ የኢትዮጵያ ገዳም አስ ረድ በኢየሩሳሌም በ፲፱፻፱ ዓ. ም.

፪ኛ ርትዕት ይእቲ ሃይማኖቶሙ ለቅዱሳን አበዊነ በ፲፱፻፲፱፪ ዓ. ም.

፫ኛ ስለ ዴር ሡልጣን የኢትዮጵያ ርስትነት በ፲፱፻፲፱፫ ዓ. ም.

፬ኛ ፩ኛ መጽሐፍ ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው በ፲፱፻፲፱፯ ዓ. ም.

፭ኛ ፪ኛ መጽሐፍ ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው ። በ፲፱፻፳፯ ዓ. ም መስከረም ፯ ቀን ።

፮ኛ ፫ኛ መጽሐፍ ማሻሻል የተለመደ ሕግ ነው በ፲፱፻፳፯ ዓ. ም ጎንደር ፲፯ ቀን ታተመ ።



መምህር ኪዳነ ማርያም
ገብረ ሕይወት ።

ዲያቆን ሰለሞን ዮሐንስ
0911860113
0111/271609
D.N Solomon Yohannes
www.ethiopianorthodox.org

ማ ረ ሚ ያ ።

ተራ ቁ.	ግድፈት	እርም	ገጽ
፩	ነነዊ ጸመ ሐዋርያት	ነነዊ ዐቢይ ጾም	
	ከሰኞ	ጾመ ሐዋርያት ከሰኞ	፭
፪	፯ቱ ጳጉሜን	፯ኛይቱን ጳጉሜን	፲
፫	፫ቋቋ	፫ደቋ	፲፪
፬	እናዳስረዱን	እንዳስረዱን	፴፪
፭	አስረዳኝ	አስረዳኝ	»
፮	፫ የደቂቃና የሰከንድ	፫ኛ የደቂቃና የሰከንድ	፴፱

www.ethiopianorthodox.org